# ጩኸቴ!!

(አሥራደው ከፈረንሳይ)



ኮከብሽ....._..... ኮከቤ:
ዕጣዬ....._..... ዕጣሽ ሆኖ፤
እኔነቴ ባንቺ:
አንቺነትሽ በ'ኔ - አብሮ ተጎናጉኖ፤

ትንፋሽሽ ትንፋሼ - ካንድ ሳንባ ሲፈልቅ፤
ልቤ አንቺን ሞሽሮ : ሲጠብብ ሲጨነቅ፤
አብረን ስንጠመቅ : ባንቺ ወዝ በኔ ላብ፤
አንቺ በ'ኔ ፈክተሽ : እኔ ባንቺ ሳብብ፤
ቅዠትሽ ቅዠቴ - ሕልሜ ሆኖ ሕልምሽ፤
ደስታዬ ደስታሽ - ሃዘኔም ሃዘንሽ፤
ጩኸቴ ብቻ ነው: ያልሆነ ጩኸትሽ፤
መስማት ተሰናቸው: ተደፍነው ጆሮችሽ::

ባንቺ አፍ ተጎርሶ - በኔ ጥርስ ሲደቅ፤
ተፈጭቶ በኔ ሆድ - ባንቺ አንጀት ሲሰለቅ፤
ድው ! ድው ! እያለ - ድንቡልቅ ድንቡልቅ፤
ልብሽ ደሙን ሲረጭ : አታሞ ሲደልቅ፤
አብሮ ተቀላቅሎ - ደምሽ በደሜ ውስጥ፤
ሲፈስ ባንቺ ገላ : የኔን ልብ ሲያቋርጥ፤
ተጠላልፎ አንድላይ - አንጀትሽ ካንጀቴ፤
ሞትሽ ሆኖ ሞቴ - መኖርሽ ሕይወቴ
ጩኸቴ ብቻ ነው : ያልሆነ ጩኸትሽ፤
መስማት ተሰናቸው : ተደፍነው ጆሮችሽ::

ማስታወሻነቷ: ላልተሰሙ ወይም ላልተደመጡ ጩኸቶች በሙሉ !!